የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፲፱
አዲስ አበባ የካቲት ፴ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

27th Year No.19
ADDIS ABABA, 9th March, 2021

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፵፪/፪ሺ፲፫

ለብሔራዊ ሜቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ የሜቲዎሮሎጂ ምልከታ መሠረተ ልማት እና የትንበያ አቅም ግንባታ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዳንስኬ ባንክ ኤ.ስ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ.................................ገጽ ፲፫ሺ፵፮

**Content**

Proclamation No.1242/2021

Danske Bank A/S Loan Agreement for financing Meteorological Observation Infrastructure and Forecasting Capabilities of the National Meteorological Agency Project Ratification Proclamation ..........................page 13046

**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፵፪/፪ሺ፲፫**

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዳንስኬ ባንክ ኤ.ስ መካከል የተደረገዉን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

የብሔራዊ ሜቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ የሜቲዎሮሎጂ ምልከታ መሠረተ ልማት እና የትንበያ አቅም ግንባታ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፰ ሚሊዮን ፰፻፰ሺ፰፻፳፱.፸፱ ዩሮ (ስምንት ሚሊዮን ስምንት መቶ ስምንት ሺህ ስምንት መቶ ሃያ ዘጠኝ ከ.፸፱ ዩሮ) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዳንስኬ ባንክ ኤ.ስ መካከል ህዳር ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

**PROCLAMATION NO. 1242/2021**

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE DANSKE BANK A/S**

**WHEREAS**, the Loan Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Danske Bank A/S stipulating that the Danske Bank A/S provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan amount of 8,808,829.79 Euro (Eight Million Eight Hundred Eight Thousand Eight Hundred Twenty Nine 79/100 Euro) for financing Meteorological Observation Infrastructure and Forecasting Capabilities of the National Meteorological Agency Project, was signed in Addis Ababa on 8th day of December 2020;

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥር ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም ባካሄደዉ ፲ኛ መደበኛ ስብሰባ ያፀደቀዉ በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "ለብሔራዊ ሜቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ የሜቲዎሮሎጂ ምልከታ መሠረተ ልማት እና የትንበያ አቅም ግንባታ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዳንስኬ ባንክ ኤ.ስ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፵፪/፪ሺ፲፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዳንስኬ ባንክ ኤ.ስ መካከል ህዳር ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ፀድቋል፡፡

**፫. <u>የገንዘብ ሚኒስቴር ስልጣን</u>**

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፰ ሚሊዮን ፰፻፰ሺ፰፻፳፱.፸፱ ዩሮ (ስምንት ሚሊዮን ስምንት መቶ ስምንት ሺህ ስምንት መቶ ሃያ ዘጠኝ ከ.፸፱ ዩሮ) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**WHEREAS**, the House of Peoples' Representative of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said agreement at its 10th regular session, held On 4th day of February, 2021;

**NOWTHERFORE**, in accordance with Article 55(1) and (12) of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "Danske Bank A/S Loan Agreement for financing Meteorological Observation Infrastructure and Forecasting Capabilities of the National Meteorological Agency Project Ratification Proclamation No.1242/2021".

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Loan Agreement signed in Addis Ababa on 8th day of December 2020 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Danske Bank A/S is hereby ratified.

**3. <u>Power of the Ministry of Finance</u>**

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of 8,808,829.79 Euro (Eight Million Eight Hundred Eight Thousand Eight Hundred Twenty Nine 79/100 Euro) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**፬. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት ፴ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**4. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazettee.

**Done at Addis Ababa, On this 9th Day of March, 2021**

**SAHILEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDRAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**